የግዕዝ ፊደላት

የመጀመሪያው ፊደል “ግዕዝ” ሁለተኛው “ካዕብ” ሦስተኛው “ሣልስ”፣ ወዘተ. በመባል ይጠራሉ፡፡ በርግጥ ፊደላቱ በዓይነት ሲሰደሩ በግሪኩ አልፋ እና ኦሜጋ፣ በእንግሊዝኛ a እና z የመጀመሪያና የመጨረሻ ፊደላት እንደሆኑ ሁሉ በግዕዝ የመጀመሪያው “ሀ ሲሆን የመጨረሻው “ፐ” ነው፡፡

ግዕዝ	ካዕብ	ሣልስ	ራብዕ	ሐምስ	ሳድስ	ሳብዕ
ሀ	ሁ	ሂ	ሃ	ሄ	ህ	ሆ
he’	hu	hi	ha	hie	h	ho
1	2	3	4	5	6	7

በተጨማሪም ተውሳክ ፊደላት (ድርብ ፊደላት) የሚባሉ አሉ፡፡ እነዚህም ቀጥሎ ተዘርዝረዋል፡፡

ቈ	ቍ	ቋ	ቍ	ቌ
ኈ	ኍ	ኋ	ኍ	ኌ
ጐ	ጕ	ጓ	ጕ	ጔ
ኰ	ኵ	ኳ	ኾ	ኴ

በግዕዝ ውስጥ የሌሉ በአማርኛ ውስጥ የሚገኙ ፊደላትም አሉ፡፡ እነዚህ የአማርኛ ፊደላት ቀጥሎ ተዘርዝረዋል፡፡ እነሱም ሸ፣ ቸ፣ ኸ፣ ጀ፣ ኘ፣ ቨ፣ እና ጨ ናቸው፡፡

2. የሣምንቱ ቀናት ስያሜ

1	2	3	4	5	6	7
እሑድ	ሰኑይ	ሰሉስ	ሮቡዕ	ሐሙስ	ሰዱስ	ሰብዕ
፩	፪	፫	፬	፭	፮	፯

ቁጥሮች

ተ.ቁ	የግዕዝ አጻጻፍ	አማርኛ	የግዕዝ አጻጻፍ	የማርኛ
1	፩	አንድ	፳	ሃያ
2	፪	ሁለት	፴	ሣላሳ
3	፫	ሦስት	፵	አርባ
4	፬	አራት	፶	ሃምሳ
5	፭	አምስት	፷	ስድሳ
6	፮	ስድስት	፸	ሰባ
7	፯	ሰባት	፹	ሰማንያ
8	፰	ስምንት	፺	ዘጠና
9	፱	ዘጠኝ	፻	መቶ
10	፲	አስር		

ተ.ቁ	የግዕዝ ቁጥር አጻጻፍ	የግዕዝ አጠራር	የአማርኛ ትርጉም
1	፲፻	ዐሠርቱ ምዕት	አንድ ሺህ
2	፲፻	ዕስራ ምዕት	ሁለት ሺህ
3	፻፻	እልፍ	አስር ሺህ
4	፲፻፻	ዐሠርቱ እልፍ	አንድ መቶ ሺህ
5	፲፻፻፻	ምዕት እልፌት	አንድ ሚሊዮን
6	፻፻፻፻	ምእልፌት	100 ሚሊዮን

<u>ትውውቅ</u>

ሰላም ለከ እኁየ	ወ ሰላም ለከ
(ሰላም ላንተ ይሁን ወንድሜ)	(ሰላም ላንተም ወንድሜ)
መኑ ስምከ እኁየ	ወልደ ገብርኤል ውእቱ ስምየ
(ስምህ ማን ነው ወንድሜ)	(ስሜ ወልደ ገብርኤል ነው)
ወመኑ ስመ አቡከ	ገ/ ማርያም ውእቱ ስመ አቡየ
(ያባትህ ስም ማን ነው)	(ያባቴ ስም ገ/ማርያም ነው)
እስፍንቱ አዝማኒከ	እሥራ ወአሐዱ
(ዕድሜህ ስንት ነው)	(ሀያ አንድ)
እም አይቴ መጻእከ	እም ጎጃም
(ከየት መጣህ)	(ከጎጃም)
ግብር እፎ ውእቱ	ሚመ ኢ.ይብል
(ሥራ እንዴት ነው)	(ምንም አይል)
እስኩ ነዓ ነሑር ኀበ ቤተ እግዚአብሔር	ትፍስሕትየ ውእቱ
እስኪ ና ወደ ቤተክርስቲያን እንሂድ	(ደስታዬ ነው)
ሕይወት እፎ ውእቱ	ሠናይ ውእቱ
(ሕይወት እንዴት ነው)	(ጥሩ ነው)
አሉ አብያኒከ ውእቶሙ	እወ
(እነዚህ ጓደኞችህ ናቸው)	(አዎ)
አይቴ ብሔሮሙ	(ዝ እም ሲዳሞ ወዝኩሰ እም ወሎ)
(የት ነው ሀገራቸው)	(ይህ ከሲዳሞ ነው ያ ደግሞ ከወሎ)
ትትሜሀርኑ ትምህርተ ዘመነዌ	እወ እትሜሀር አነ ትምህርተ ዘመነዌ
(የዘመናዊ ትምህርት ትማራለህ)	(አዎ የዘመናዊ ትምህርት እማራለሁ)
አይቴ ውእቱ ቤተ ትምህርትከ	ወሊ.ጋ ዩኒቨርሲቲ ውእቱ ቤተ ትምህርትየ
(ትምህርት ቤትህ የት ነው)	(ወሊጋ ዩኒቨርሲቲ ነው ትምህርት ቤቴ)
ስፍነ አመተ በጻሕከ	ሰልሰ አመተ በጻሕኩ
(ስንተኛ ዓመት ደረስክ)	(3 ዓመት ሆኖኛል)
ተአምርኑ ትምህርተ ሀገርከ	ምንት ውእቱ ትምህርተ ሀገርየ
(የሀገርህን ትምህርት ታውቃለህ)	(የሀገሬ ትምህርት ምን ነው)

ተውላጠ ስማዊ መስተዓምራን

በግዕዝ አሥር የሚሆኑ ተውላጠ ስሞች አሉ፡፡

	ግዕዝ	አማርኛ
1.	አነ	እኔ
2.	አንተ	አንተ
3.	አንቲ	አንቺ
4.	ውእቱ	እሱ
5.	ይእቲ	እሷ
6.	ንሕነ	እኛ
7.	አንትሙ	እናንተ (በቅርብ ለሚገኙ ወንዶች)
8.	አንትን	እናንተ (በቅርብ ለሚገኙ ሴቶች)
9.	ወእቶሙ	እነዚያ (ወንዶች)
10.	ውእቶን	እነዚያ (ሴቶች)